## እንኳን ደሕና መጡ የኔ ጌታ !

ምስራቅ ምዕራብ ብለዉ
ካዲሱ ዓለም ቃል ገብተዉ
እላይ የወጣን እታች አግብተዉ
ጎረቤትን በጎረቤት ዘብ አቁመዉ
ኧረ እንዴት ያለዉን አምክነዉ
ለዘር ዘር ማዳበሪያ ብለዉ
ሠማይና መሬትን ነፃ አዉጥተዉ
እግዜር እርስዎን ባይሰጠን
ከቶ የት ነበር መድረሻችን
ዓለማዊ አይደሉ ቅዱስ
ዉግዝ ከመ አርዮስ

## እንኳን ደሕና መጡ የኔ ጌታ !

ከአንሸር ሆጃ አሉ ኮኹን
ስም አጥፊ ትምክተኞች
የባዶ ስድስት ሱሰኞች
የቀይ ሺብር ትርፍራፊዎች
ዛሬም ሟች ሆነዋል
አሉል አካድር ብለዋል
ይበሉት የኔ ጌታ የምን ዴሞክራሲ ነው
ለነገሩ የባዕድ ቋንቋ ነዉ
ይንገሯቸዉ ለነዚህ የሁለት ብትር ቁስለኞች
የሕብረተሰብ ደዌ ግዞተኞች
ደሞ ሰላምና እርቅ ይላሉ
ወኔዎትን ሲከጂሉ
የማንን ዙፋን ማን ሊወስድ?
ይዋደቋታል እንጅ
የትግራይ ጉድጓዶች አብጠዉ ይፈንዱ እንጅ
ዙፋኑ የርስዎ ነዉ
ጃንሆይ ባጥንትዎ ነዉ
ያገኙት በረሃ ከርመዉ
አዋግተዉ ወዲህ ብለዉ ወዲያ ብለዉ
አባት ጓዶችን አስቀይመዉ
ስንቱን ሕልም ቅዠት አርገዉ

## እንኳን ደሕና መጡ የኔ ጌታ !

ደሞ እድሜ ለዋሺንግተን ሲሉ
እርስዎ የነበሩ አድዋ
በየት ብለዉ እንዴት አርገዉ?
ዋሺንግተንን ከየት አምጥተዉ?
ደጋግመዉ ያበሰሩትን
ፍፁም የማይታሙበትን
በጓዳ በር መግባትን
ከጠላት መዶሌትን

## እንኳን ደሕና መጡ የኔ ጌታ !

«አናርኪስት» ይሁን «ትምክተኛ»
ሲሆንብዎ መጋኛ
ብዕር ሲቀስር በርስዎ
ምላጭ መሳብ ነዉ ግዴታዎ
ለመንጌ ሰርቶለታል
እርስዎስ ምን ያንስዎታል?
ለተቃዋሚ አይራሩ
አሳደዉ ኩቴዉን ይስበሩ
ኬንያ ይግባ ሱዳን
ዩጋንዳ ይሁን ጅቡቲ አሊያም ሱማሌ
ሰዉ ይላኩ አልባሌ
በርስዎ ላይ የሚቃጣ
ሲሸተዉ ነዉ የሞት እጣ
ድምፁ ረጭ ይበል በደፈጣ

## እንኳን ደሕና መጡ የኔ ጌታ !

አይደሉ ታሪካዊ አደጋ
ደም የሸተተዉ የጅብ መንጋ
ሐድጊ ያለ ሳይነጋጋ
ማን ነዉ የሚከስዎ?
ማን ነዉ የሚፈርድዎ?
ሺህ በክንፉ ሺህ ባክናፍዎ
ሰሜን ከፊት ምዕራብ ከጀርባዎ

አለበል (3/15/86 EC)